# ክቡር መስቀል

ሁብተ ሥላሴ ላኛቸው

መስቀል ለክርስቲያኖች የሕይወትና የድኅነት ምልክት ስለሆነ ቃሉ ዘወትር በኅሊናችን ይደውላል፤ በአንደበታችን ይነገራል፤ ስዕሉና ተግባሩ ከዓይናችን ፊት አይሠወርም። በጸሎታችን መጀመሪያና በጸሎቱ መካከል ነገረ መስቀሉን የሚነካ ቃል ሲነግ ወይም የሚያስደነግጥና ለሕይወታችን ተስማሚ ያልሆነ መጥፎ ነገር ሲያጋጥም እናማትባለን፤ ስመ እግዚአብሔር እየጠራን ሰውነታችንን በመስቀል ምልክት እንባርካለን። በመሆኑም ስለመስቀል የሚጻፈው፣ የሚነገረውና የሚባለው ሁሉ አዲስ አይሆንም።

## መስቀል ቅድመ ልደተ ክርስቶስ

መስቀል በመስቀልነቱ የታወቀው፤ የዓለም መድኅን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤዛ ዓለም ከተሰቀለበት ወዲህ ብቻ አይደለም።

ሰውን በስቅለት መቅጣት (በመስቀል መስቀል) የተጀመረው በጥንቱ ፋርስ በመባል ይታወቅ በነበረው አገር እንደሆነ የታሪክ ሰዎች ጽፈዋል። ፋርስ የሚባለው አገር ቅድመ ልደተ ክርስቶስ (፭፻፶፱—፫፻፴፩) በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ታውቆና ደምቆ የነበረ ግዛት እንደነበረ ይነገራል። የጥንቱ ፋርስ የግዛት ክልል በስተምሥራቅ «ኢንደስ» ከሚባለው፣ በምዕራብ ከታላቁ የጤግሮስ ወንዝ ሠፈውን የጺጋና ሜዳማ ሥፍራ የያዘው ክፍል ሲሆን፤ በዛሬው ጊዜ በኢራን ምድር የተካተተ ነው።

በጥንቱ ፋርስ «የመሬት አምላክ» ተብሎ የሚመለክ የማይታወቅ አምላክ ስለ ነበር በማኅበረሰቡ ሕይወት በማጥፋት ተወንጅለው በሞት የሚቀጡ ሰዎች ቅጣታቸውን በምድር ላይ የተቀበሉ እንደሆነ የመሬት አምላክ ክብር እንዳይረክስ ለመጠንቀቅ ሲባል ወንጀለኞች ከምድር ከፍ ባለ መስቀል ተሰቅለው እንዲሞቱ ይደረግ እንደ ነበር ይታወቃል።

ይኸው ዓይነት ቅጣት ወደ ሮም የተዛመተውም ከዚሁ አካባቢ እንደሆነ ይነገራል።

የመስቀል ሞት (የስቅላት ቅጣት) ቀደም ባሉት አገሮች በግሪክ፣ በሮም፣ ኋላም በአሶር፣ በግብፅ፣ በካርታጎ፣ በሕንድና በጀርመን ተስፋፍቶ ይሠራበት ነበር።

ታላቁ እስክንድር በጦር እየጋለበ ያስጨንቃቸውና ያስገብራቸው ከነበሩ አገሮች አንዷ የጢሮስ ከተማ ወረራውን ለመመከት ባደረገችው መቋቋም ድል ከሆነች በኋላ በወሰደው የበቀል ርምጃ ፪ ሺህ ያህል ጢሮሳውያን በስቅላት ሞት እንዲቀጡ ተፈርዶባቸዋል።

ስቅላት በግብፃውያንም የተለመደ ነበር። (ዘፍ.፵፥፲፱) በወቅቱ ሕዝብ አመለካከትና ውሳኔ የተጣሉና የተወገዙ ወንጀለኞች መቅጫ በሆነው ስቅላት ሮማውያንን መቅጣት አሳፋሪ ነበር። በዘርና በደም ሮማዊ የሆነውን ዜጋ ሁሉ በመስቀል እንዳይቀጣ መለየት (ነፃ ማድረግ) የተለየ የዜግነት ክብር መግለጫ ነበር። የስቅላት ሞት የሚፈረድባቸው ሰዎች ተሰቅለው ከመሞታቸው በፊት ቅጣቱን ለማክበድ የሚደርስባቸው ተጨማሪ ስቃይ ነበረባቸው። በገመድ መታሠርና በጅራፍ መገረፍ፣ በዱላና በጥፊ መደብደብ፤ ሰብአዊ ኅሊናን የሚዘገንን የስቃይ ምርመራ መቀበል፣ በአደባባይ መጐተትና መዋረድ፣ የሚሰቀሉበትን ግንድ (እንጨት) ተሸክሞ ወደ ሞት መንዳት ልብስን ተገፎ እርቃንን መሰቀል፣ በመስቀል

ረጉና ዓለምን በደሙ ለመቀደስ የተነገረው ትንቢትና በትንቢቱ መሠረት የተጠበቀው ጊዜ በመስቀሉ ተፈጽሟል። ከዚያ ወዲህ መስቀል የመርገምና የወንጀል ምልክት መሆኑ ቀርቶ በማዕከለ ምድር የቆመ፣ የኃጢአት ጨለማ የተወገደበት የብርሃን ዐምድ ሆኖአል። ዐምድ ቤት ያጸናል። መስቀልም የምእመናንን ልቡና በሃይማኖት ያጸናል። በተስፋ ያበረታል። ስለሆነም መስቀል በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ታላቅ ክብር አለው።

መስቀል ከሁሉ ነገር ለተለዩ፣ ለተቀደሱና ለከበሩ ነገሮች ሁሉ መለያ ሆኖአል። ስመ እግዚአብሔር ተጠርቶ በመስቀል የተባረከ ነገር ሁሉ የነጻ የተቀደሰ ነው።

## የመስቀል በዓል

በቤተ ክርስቲያን ከታወቁት ዐበይት (ታላላቅ) በዓላት አንዱ የመስቀል በዓል ነው።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል የዕውራንን ዐይን እያበራ ልዩ ልዩ ደዌ ያደረባቸውን ሕሙማንን እየፈወሰ ተአምራት በማድረጉ በሰቀሉት ሰዎች ዘንድ ባሳደረው ቅንዓት፣ በአልባሌ ሥፍራ ተጥሎ፣ በከተማ ጉድፍና ጥራጊ ማከማቻ ውስጥ ተቀብሮ ለ፫፻ ዓመታት ያህል ከቆየ በኋላ ተፈልጎ በመገኘቱ ታሪካዊ መታሰቢያው በየዓመቱ ይከበራል።

ቅዱስ መስቀሉ የተገኘው በቆስጠንጢኖስ እናት በእሌኒ እግሚኢይነት በተደረገ ፍለጋ ሲሆን በዓሉ የሚከበረው ይህንኑ ለማስታወስ ነው።

እሌኒ ከመንፈሳውያን አበው በተነገራት መሠረት ያዘጋጀችው የደመራ እንጨትና በደመራው ላይ የተደረገው የዕጣን ጢስ ወደላይ ወጥቶ ተመልሶ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ አመልክቷል። በዚያው ላይ ቁፋሮ ተካሂዶ መስቀሉ ተገኝቷል። ያንን ትርኢት ለማስታወስ መስከረም ፲፯ ቀን በዋዜማው ደመራ ይደመራል፣ ጸሎተ ወንጌል ይደርሳል፣ መዝሙርና ሽብሸባ ይደረጋል፣ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይቀርባል።

መስከረም ፲፯ ቀን ቁፈር የተጀመረበት፣ መስቀሉ ተገኝቶ ከወጣ በኋላ በስሙ በተሠራው ቤተ መቅደስ የገባበትና ቅዳሴ ቤቱ የተከበረበት በስብሐተ እግዚአብሔርና በመንፈሳዊ ሥርዓት ይከበራል።

መስቀሉ ተቆፍሮ ከተገኘበት የወጣው መጋቢት ፲ ቀን ሲሆን በወርኃ ጾም ተድላ ደስታ ማድረግ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተከለከለና የመስቀልን በዓል በዐቢይ ጾም ማክበር የማይቻል በመሆኑ ቁፋሮው በተጀመረበትና ቅዳሴ ቤቱ በተከበረበት በመስከረም ፲፯ ቀን እንድነት እንዲከበር አበው ወስነዋል።

መስቀሉ ከተቀበረበት ቦታ በተገኘ ጊዜ አብረው ተቀብረው ከነበሩት የሁለቱ ወንበዴዎች (የፈያታይ ዘየማንና ፈያታይ ዘፀጋም) መስቀሎች የጌታ መስቀል ሊለይ የቻለው እንደተለመደው ሕሙማንን በማዳኑና ተአምር በማድረጉ ነው።

<u>ችቦ የሚበራበትም በሦስት ታላላቅ ምክንያቶች ነው።</u>

፩. እንደ ዛሬው በሰው ልጆች የዕውቀት መሻሻል በጥበብ ምርምርና የፈጠራ ውጤት የተሟላና የተመቻቸ የመገናኛ አገልግሎት (ኮሙኒኬሽን) ባልነበረበት በቀድሞው ዘመን በየተራራው ላይ መብራት በማሳየት የነበረውን የዜና ማስተላለፊያ ዘዴ በመጠቀም መስቀሉ በተገኘ ጊዜ የምሥራቹን ዜና ከኢየሩሳሌም እስከ ቁስጥንጥንያ ለንጉሡ ለቆስጠንጢኖስና ለሕዝቡ ለማድረስ የተደረገውን ቅብብሎሽ ያዘክራል።

፪. በሌላ ታሪክና ጊዜ ህርቃል የተባለ ንጉሥ ቅዱስ መስቀሉን በአመድ ለውሶ ከነበረበት አገርና ከማያምኑበት ወገኖች አስመልሶ በዝኆኖች በሚሳብ ሠረገላ ተቀምጦ መስቀሉን በፊቱ አድርጎ ቁስጥንጥንያ በገባ ጊዜ ሕዝቡ ችቦ እያበራ በሆታና በእልልታ ያደረገለትን አቀባበል፣ ለቅዱስ መስቀሉ የነበረውን ክብር ያመለክታል።

፫. ኢትዮጵያዊው ንጉሥ አፄ ዳዊት ግማደ መስቀሉን (የመስቀሉን ቀኝ ክንፍ ስባሪ) በብዙ ጥበብ ወደ ኢትዮጵያ አስመጥተው ሀገራችን በገባ ጊዜ ሕዝቡና የወታደሩ ሠራዊት እየተመመ የሚንተገተግ የችቦ መብራት እያበራ በሆታና በእልልታ ካህናት በዝማሬና በይባቤ ያደረጉትን ታሪካዊ አቀባበል ያሳያሉ። በተለይ ይህኛው በዓል «የአፄ መስቀል፣ ተቀጸል ጽጌ» እየተባለ መስከረም ፲ ቀን በያመቱ በቤተ መንግሥት በታላቅ ድምቀትና መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ሲከበር ኖሯል።

በአፄ ዳዊት የመጣው ግማደ መስቀል መጀመሪያ በመናገሻ ተራራ ምዕራባዊ እርከን ላይ በምትገኘው እምባ (መናገሻ) ማርያም ገዳም ከረፈ በኋላ ለዘለቄታው እንዲቀመጥ የተወሰነው ቦታ ሌላ በመሆኑ በራእይና በልዩ ልዩ ሁኔታ በተገለጸው ምልክት መሠረት በተፈጥሮ አቀማመጧ የመስቀል ቅርጽ (ዕይታ) ባላት በግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ገዳም ተወስዶ እንዲቀመጥ ተደርጓል። ታሪኩ በዚያው ገዳም «ጤፉት» በተባለ መጽሐፍ ይገኛል። ሊቃውንቱም በቃል እያሳመሩ ይገልጹታል።

በዚህ መልኩ ስለ ቅዱስ መስቀሉ ፍለጋ በእሌኒ የተደረገውን ዝግጅትና ምልክት፣ ከዚያም በኋላ በየዘመኑ

ላይ የሚመርና የሚጐመዝዝ፣ (የሚሆ መጥጥ) ፈሳሽ መጋት በመጨረሻም ጎንን በጦር መወጋትና አጥንቶችን መስበር፣ መዘባበቻና መሳለቂያ መሆን የመሳሰለውም የጭካኔ ሥራ ዎች ሁሉ «ወንጀለኛ» ተብለው በሰው እጅ በሚወድቁ ሰዎች ላይ የሚደርስ በደል ነበር። (ዮሐ.፲፱፥፩፣ ዮሐ.፳፯፥፲፱–፳፭)


የስቅላት ቅጣትና ሞትን አስመ ልክቶ በጥንቱ አይሁድ ኅብረተሰብ ልማድ የሚወሳው ታሪክ እንደሚ ገልጸው፣ ቅጣቱ የተወሰነበት ሰው በግርፋትና በውግራት ከተገደለ በኋላ እጆቹን ከራሱ በላይ ቀጥ ካለ እንጨት ጋር አስሮ ወይም በችንካር ጠርቆ ማቆም ወይም አራት ማዕዘን ተመሳ ቅሎ በተዘጋጀ እንጨት ላይ የእጅ መዳፎችን፣ የእግር ጫማዎችንና ራስን ቸንክሮ መስቀል፣ እስከ ጀንበር ጥልቀት ሰቅሎ ማዋል የታወቀ ነበር። (ዘኁ.፳፭፥፬)

በዚህ መልኩ ሰዎች በመስቀል ላይ ሲሞቱ ከጀንበር መጥለቅ በኋላ ግን የሞቱትን ሰዎች በመስቀል ላይ ማሳደር በጥብቅ የተከለከለ ነበር። (ዘዳ.፳፩፥፳፫)

የስቅላት ሞት በርግጥም ሆነ በአይሁድ ዘንድ አስታቂ የሚጠላና የሚያስፈራ የቅጣት ዓይነት ነበር። ይልቁንም በአይሁድ ማኅበረሰብ የመስቀል ሞት የመጠላትና የመርገም ምልክት ነበር። በመስቀል የሚሞቱ ሰዎች ሁሉ በሰውም በእግዚአብ ሔርም የተጠሉና የተረገሙ ተብለው ይቆጠሩ ነበር። (ዘዳ.፳፩፥፳፫)

ስለመስቀል ምንነትና መሠረታዊ አመጣጥ ስንመረምር ወደጥንተ ፍጥረት ይሰበናል። በዓለመ መላእክት ስድስት ክንፍ ያላቸው ሱራፌል «በሁለት ክንፋቸው ፊታቸውን በሁለት ክንፋቸው እግራቸውን ይሸፍ ናሉ፣ በሁለት ክንፎቻቸው ይበራሉ» የሚለው አገላለጽ የመስቀል ቅርጽ እንደሚያመለክት እንረዳለን። (ኢሳ.፮፥፪)

በግብሩ ከማኅበረ መላእክት የተለየው ሳጥናኤልን ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤልና ሠራዊቱ በሰማይ በተዋጉት ጊዜ ለቅዱሳን መላእክት



ተሰጥቶ የነበረው የኀይልና የድል ምልክት መስቀል እንደነበር አበው ሊቃውንት በትርጓሜ መጻሕፍት ይገልጻሉ። እጆቻችንን በምንዘረጋበት ጊዜ የ«ተ» ፊደል ዕይታ ያለው የሰውነታችን አቋም የመስቀል ቅርጽ ይሰጣል። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ነገር ክቡር መስቀል በጥንተ ፍጥረት ጀምሮ የድልና የሕይወት ምልክትነቱ ታውቆ የሚኖርበት ምሥጢራዊ ክስተት እንደነበረው ነው። (ራእ.፲፪፥፯) ለቆስጠንጢኖስ በአየር ላይ ተቀርጾ የታየው የድል ምልክትም ይኸው ነበር።

ዓለም በኀጢአት ሥራ ተበላሽቶ ሥጋ የለበሰና የሕይወት እስትንፋስ ያለው ተንቀሳቃሽ ፍጡር ሁሉ ከምድረ ገጽ እንዲጠፋ ማየ ድምሳሴ (የጥፋት ውኃ) በተዘጋጀለት ጊዜ ለሰው ዘር መዳንና መትረፍ ምክንያት የሆነው የኖኅ መርከብ የተሠራበት እንጨት (ዘፍ.፮፥፲፬)፣ ነቢየ እግዚአ ብሔር ሙሴ የግብፅን መሰግላንና መናፍስት ጣሪያዎችን ያሳለፈበት፣ ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ እሥራኤልን በደረቅ ምድር ያሻገረባት የኀይል ምልክት በትር የመስቀሉ ምሳሌዎች እንደነበሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያመሠጥራሉ። (ዘፀ.፯፥፰–፲፫፣ ፲፬፥፲፮)።

የኖኅ መርከብ ማየ ድምሳሴ፣ ማየ ሥራዊ (የጥፋት ውኃ) ከተፈረደበት ሕዝብ ለሰው ዘር መትረፍ ምክንያት የሆኑ ስምንት ሰዎች ድነውበታል። የሙሴ በትርም ጠንቋዮችና አስማተ ኞችን አሳፍራ ባሕረ ኤርትራን ለማሻ ገር ለእሥራኤል ዘሥጋ ምክንያተ ሕይወት ሆናለች። ትእምርተ ሕይ ወት፥ ትእምርተ መዊዕ (ድል) ዕፀ መስቀልም በክርስቶስ አምነው የሚ ያማትቡበት፥ የሚስሙትና የሚዳስ ሱት እሥራኤል ዘነፍስ (ክርስቲያኖች ምእመናን) ከክህደት፣ ከአምልኮ ጣዖት ድነውበታል። ደዌ ሥጋና ደዌ ነፍስን አስወግደውበታል። የቤተ ክርስቲያን መቋሚያም የመስቀል ምሳሌ ነው።

## የክርስቶስ መስቀል

የዓለም መድኅን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከበደላችን ያነጻን ዘንድ በወንጀለኞች መካከል እንደወንጀለኛ ተቆጥሮ በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቅ ሏል። በመስቀሉ ሰላምን ስለማድ

በነበሩ ነገሥታት ሲፈጸም የነበረውን የአከባበር ሥርዓት ሁሉ ለማስታወስ በየቦታው ደመራ ይደመራል፤ በደመራው ዕለትና ሥፍራ ስብሐተ እግዚአብሔር ይደርሳል ሕዝቡ «ኢዮሀ አበባዬ መስከረም ጠባዬ» እያለ ከጥቢ ጋር የተያያዘ ዝማሬ በማቅረብ በእልልታና በሆታ ያከብረዋል።


ደመራው በችቦ እሳት ተለኩሶ አመድ እስኪሆን ይቃጠላል ከማታው ጀምሮ እስከ ማለዳው ጠዋት ድረስ ሕዝቡ አመዱን በራቁት እግሩ ይረግጠዋል፥ በእጁ ጣት ግንባሩን በመስቀል ምልክት በአመዱ ይኳለዋል (ይቀባዋል)፥ ትርኳሹን እየተሻሙ ወደየቤቱ ይወስደዋል። ታላቅ የእምነት መግለጫ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሁሉን ይባርካል፤ ይቀድሳል ያነጻል። ደመራውም የተጸለየበትና የተባረከ ስለሆነ መድኀኒት ነው። ለሰው ብቻ ሳይሆን ለእንስሳትም አመዱን ያሹበታል ይግቷቸዋል። ቅዱሲ የተቀደሰበት ሕራረ ዕጣን (የዕጣን እራሪ) በእምነት እየወሰዱ ለሕሙማን መጠቀም በቤተ ክርስቲያናችን የተለመደ ነውና።

## መስቀል የሕይወት ምልክት

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው መስቀል ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የወንጀለኞች መቅጫ ሆኖ በሚያስቅቅና በሚያስደንግጥ መልኩ ሲታይ ኖሯል። በመስቀል የሚሞቱ ሁሉ የተረገሙና የተወገዙ ነበሩ። የዓለም መድኀን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰቀለበትና ክቡር ደሙን ካፈሰሰበት ወዲህ ግን የነጻነት ዐዋጅ የታወጀበት ዙፋን ስለሆነ የሕይወትና የድኅነት ምልክት ሆኖ አል። መስቀል ለሚያምኑበትና ለሚጠቀሙበት ሁሉ በብርሃንና በጨለማ፤ በሕይወትና በሞት መካከል የቆመ የሰላም ምልክት የሕይወት ዓላማ ነው።

የእግዚአብሔርን ሕጉን ጠብቀው ትእዛዙን አክብረው የሚፈጽሙና በአምልኮቱ ጸንተው የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ከጥፋትና ከክፉ ነገር የሚጠበቁበት ይህ የኃይልና የድል መገሪያ የሆነው የሕይወት ምልክት ይሰጣቸዋል።

ቅዱስ መስቀል አጋንንትን የሚያርቅ! መናፍቃንን የሚያስፈራ! ፍትወታቱ እኩያትን (ፈቃደ ሥጋትን) ድል የሚነሳ የሞት መቅጫ መገሪያ ስለሆነ ሀብተ ክህነት የተሰጣቸው አበው ከፉ መንፈስን ሁሉ ይገዙበታል፤ ምእመናንን ይባርኩበታል።



ሀብተ ጸጋን ያሳድሩበታል፤ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን ያሳድሩበታል።

መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ ብዙ ሰዎች የልብሱን ጫፍ ብቻ ብንዳስስ እንድናለን እያሉ ይለምኑት ነበር። «የዳሰሱት ሁሉ ዳኑ» ተብሎ እንደተጻፈ እጁን በመጫንና ወደርሱ ቀርበው የልብሱን ጫፍ (ዘፈረ ልብሱን) በእምነት የዳሰሱትን ሁሉ እንደ ፈወሳቸው ልዩ ልዩ ጸጋና በረከትም እንዳሳደረባቸው፤ ቅዱሳት እጆቹን ዘርግቶ ዓለምን በፍቅሩ በሳበበትና ወደ ድኅነት በጠራበት በክቡር መስቀሉ እየተዳሰሱና እየታሹ ምእመናን ይድኑበታል። በራኢ በብሉያትም በሐዲሳትም የታወቀ ነው። (ዘኁ. ፳፥፭፱፤ ማር.፲፥፲፪፤ ሉቃ.፭፲፥፶)

መስቀል ለክርስቲያኖች የሕይወት ምልክት ስለሆነ በአንገታችን እናስረዋለን። ይልቁንም በዘመናችን የክርስቲያኖች የኪን ጥበብ ሁሉ ምልክቱ መስቀል ሆኗል። ክርስቲያኖች በመጻሕፍታቸው በልብሳቸውና በቤት ዕቃቸው ሁሉ የመስቀል ምልክት አለበት። ቀደም ባለው ጊዜ በፈረስ ዕቃ፤ በጦር ጉረር፤ በጋሻና በእርሻ መገሪያዎች ላይ ሁሉ የመስቀል ምልክት ነበር። ዝምዝሙ፤ ጌግጌጡ ሁሉ የመስቀል ቅርጽ አለው ይሁን እንጂ መስቀል በሕይወት ምልክትነቱ ሥራ ሊሠራ የሚችለው በፍጹም እምነት እንጂ በጌጥነቱ ብቻ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። መስቀልን በሕይወተ ሥጋ ሳለን ብቻ ሳይሆን ከሞትንም በኋላ አጽማችን በሚያርፍበት መካነ መቃብራችን ላይ ሁሉ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ተቀርጾ ምልክትነቱ ይኖራል። የመከራ ሳይሆን የድልና የትንግኤ ምልክት ስለሆነ ነው።

ይህንንም በምናደርግበት ጊዜ ሁሉ «መስቀሉን ተሸክሞ የማይከተለኝ ሊያገለግለኝ አይችልም» ተብሎ የተጻፈውን የሕይወት ቃል መጠበቃችን የክርስቶስን ፈለግ መከተላችን ያሳያል። (ማቴ.፲፥፴)

በክርስቶስ አምና በቅዱስ መስቀሉ ምልክትነት የሚጠቀም ሁሉ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ አለው።

«የመስቀሉ ነገር ባለመኑ ሰዎች ዘንድ ስንፍና ነው፤ ለኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው።» (፩ቆር.፩፥፲፰) ✣

ወስብሐት ለእግዚአብሔር